# ደንብ

**የሞንትጎሞሪካውንቲፐብሊክስኩልስ**

---

ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች፡- COA-RB, DJA-RA, ECK-RA, GCA-RA, GCC, GCC-RA, IJA-RC, IRB-RA, JHC, JHC-RA

ኃላፊነት የሚመለከታቸው ክፍሎች፡ የሰራተኞች አስተዳደር እና የችሎታ ማበልፀጊያ ክፍል፤ የትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ ክፍል፤ የፋይናንስ አስተዳደር ክፍል

## የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞችን፣ MCPS አዲስ የሚቀጠሩ እጩዎችን፣ ኮንትራክተሮችን እና የበጎ ፈቃደኞችን የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት

I. ዓላማ

A. ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች፣ኮንትራክተሮች፣ እና በጎ ፈቃደኞች በወቅቱ የተፈፀሙ ጥቃቶችን፣ በደሎችን፣ እና ቸልተኝነትን ስለመለየት፣ ሪፖርት ስለማድረግ፣ እና ስለመከላከል የሥልጠና መስፈርቶችን ማዘጋጀት እና ለሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች፣ ስራ ለመቀጠር የቀረቡ እጩዎች፣ ለኮንትራክተሮች እና ለበጎ ፈቃደኞች የቀድሞ ታሪካቸውን/ዳራ የማጣራት መስፈርቶችን ማዘጋጀት።

B. የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡-

1. የጣት አሻራ በመውሰድ የተመዘገበ ብሔራዊ እና የስቴት የወንጀል ታሪክ ካለ ማጣራት፤ እና

2. አንድ ግለሰብ በሕፃናት ጥቃት ወይም ቸልተኝነት ጉዳይ ምርመራ የተደረገበ(ባ)ት መሆኑን ወይም በምርመራ ላይ የሚገኝ/የምትገኝ መሆን/አለመሆን ወይም ማስረጃ መኖር/አለመኖርን ለማወቅ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ (MCDHHS) የህፃናት ደህንነት አገልግሎት (በተለምዶ የህፃናት ጥበቃ አገልግሎቶች [CPS] በመባል የሚታወቀው) ነጻ ስለመሆኑ(ኗ) ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት።

## II. ትርጉም

A. ለዚህ ደንብ ዓላማ *የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት* ማለት የግለሰቡ(ቧ)ን የጣት አሻራ በመውሰድ ብሔራዊ እና የስቴት የወንጀል ታሪክ እንደሌለበ(ባ)ት ማጣራት ማለት ነው። በሌላ ሁኔታ ተገልጾ ካልሆነ በስተቀር፣ ሂደቱ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በኩል መጠናቀቅ ያለበት ሲሆን በሜሪላንድ ስቴት የህግ ዳታቤዝ ውስጥ የወንጀል ፍትህ መረጃ ስርዓት (CJIS) በኩል ሙሉ የጣት አሻራ የወንጀል ድርጊት ሪከርድ ማጣራትን ማካተት አለበት። MCPS የወንጀል ድርጊት ታሪክ/ዳራ ውጤት የሚያገኘው ከሜሪላንድ ስቴት እና ከፌዴራል የምርመራ ቢሮ "Rap Back" (ከታች ይመልከቱ) ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ በሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ይደርሰዋል። CJIS የወሲብ ጥቃት የፈፀሙ ወንጀለኞችን ክትትል ያካትታል። "Rap Back" ለተሳታፊ ኤጀንሲዎች የማሳወቂያ ሂደቱን በቀጥታ ያሳውቃል።

B. CPS *ከወንጀል ነጻ መሆንን ማጣራት* ማለት ግለሰቡ(ቧ) በልጅ ጥቃት ወይም ቸልተኝነት ጉዳይ ላይ የተገለጸ፣ የተረጋገጠ የወንጀል ድርጊት መፈጸም/አለመፈጸም ለማረጋገጥ CPS የአንድ ግለሰብ መረጃ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ለህፃናት ደህንነት ጥበቃ ክፍል (በተለምዶ የህፃናት ጥበቃ አገልግሎት [CPS] በመባል የሚታወቀው) የግለሰብን ማስረጃ መስጠት ማለት ነው። CPS የክሊራንስ ማጣራት የሜሪላንድ የህፃናት ኤሌክትሮኒክ ማህበራዊ አገልግሎቶች የመረጃ ልውውጥ (MD CHESSIE)፣ በስቴት አቀፍ አውቶሜትድ ኬዝ ማኔጅመንት ሲስተም፤ የዲፓርትመንቱ የደንበኛ መረጃ ሲስተም (CIS)፤ ወይም የህጻናት ጥቃት እና የቸልተኝነት ምርመራዎችን በተመለከተ መረጃ የያዘውን የማዕከላዊ መረጃ ቋት፣ CIS ወይም ሌላ ሚስጥራዊ የኮምፒዩተር ዳታቤዝ አካል የሆነውን ግምገማ ሁሉ ያካትታል።

C. *ጥፋተኛ የሚያሰኝ የወንጀል ድርጊት* ማለት በሜሪላንድ የተብራራ ሕግ (የሜሪላንድ ሕግ)፣ የትምህርት አንቀጽ፣ § 6-113 ውስጥ የተገለጸ የወንጀል ድርጊት የሚከተሉትን ያካትታል፦

a) በሜሪላንድ ኮድ የወንጀል ህግ አንቀፅ § 3-307 ወይም § 3-308 ስር የሶስተኛ ወይም አራተኛ ድግሪ ፆታዊ ጥቃት ወይም በሌላ ስቴት ህጎች መሠረት ጥቃት የተባለ እና በሜሪላንድ የወንጀል ህግ አንቀፅ § 3-307 ወይም § 3-308 ስር ጥቃት ተብሎ የተገለፀ ነው።

b) በወንጀል ሕግ አንቀጽ § 3-602 መሠረት የሕፃናት ወሲባዊ ጥቃት ወይም በሌላ ስቴት ሕጎች መሠረት በሜሪላንድ ውስጥ ከተፈጸመ በወንጀል ሕግ አንቀጽ § 3-602 መሠረት የሕፃናት ወሲባዊ ጥቃት ወንጀል፤ ወይም

c) በወንጀል ሕግ አንቀጽ § 14-101 ላይ እንደተገለጸው የዓመፅ/የረብሻ ወንጀል ወይም በሌላ ስቴት ሕጎች መሠረት እንደ ወንጀል የተገለፀ እና በሜሪላንድ ውስጥ ከተፈጸመ የወንጀል ሕግ አንቀጽ § 14-101 የሚጥስ ወንጀል፣ የሚከተሉትን ያካትታል—

1) ጠለፋ፣

2) ቤት ወይም ህንጻ የማቃጠል ወንጀል የመጀመሪያው ዲግሪ፣

3) አፈና፣

4) ሳያውቁ ሰው መግደል፣ ያለውዴታ/የግዴታ ካልሆነ በስተቀር

5) ብጥብጥ፣ ማፈራረስ፣ አካልን የመቆራረጥ ጥቃት

6) አካል ማጉደል፣

7) ግድያ፣

8) አስገድዶ መድፈር፣

9) ዝርፊያ፣

10) የመኪና ስርቆት፣

11) በጦር መሣሪያ አስፈራርቶ መኪና መዝረፍ

12) ወሲባዊ ጥቃት የመጀመሪያ ድግሪ

13) ወሲባዊ ጥቃት ሁለተኛ ድግሪ

14) በሽጉጥ በማስፈራራት ከባድ ወንጀል ወይም ሌላ የዓመፅ/የረብሻ ድርጊት መፈጸም፣

15) በሕፃናት ላይ ጥቃት መፈፀም፣የመጀመሪያ ድግሪ

16) ለአካለ መጠን ያልደረሰ(ች) ልጅ ላይ የተፈፀመ ወሲባዊ ጥቃት፣

17) በዚህ ዝርዝር ውስጥ ከአንቀጽ 1 እስከ 16 የተገለጹትን ወንጀሎች ለመፈጸም የተደረገ ሙከራ፣

18) በወንጀል ሕግ አንቀጽ § 3-315 መሠረት ከአንድ ልጅ ጋር የሚደረግን ምግባር በመቀጠል፣

19) ጥቃት መፈርጸም የመጀመሪያ ድግሪ፣

20) የግድያ ሙከራ ጥቃት፣

21) አስገድዶ ለመድፈር በማሰብ የሚፈፀም ጥቃት፣

22) ለመዝረፍ በማሰብ የተፈፀመ ጥቃት፣

23) ወሲባዊ ጥቃት ለመፈጸም በማሰብ የተደረገ ጥቃት የመጀመሪያ ድግሪ እና

24) ጾታዊ ጥቃት ለመፈጸም የተደረገ ድብደባ ሁለተኛ ድግሪ።

D. *ዲስትሪክት አቀፍ የሥነ ሥርዓት/ህግ አክባሪነት ስልጠና* ማለት እያንዳንዱ ሠራተኛ ጎልማሶችና ተማሪዎች ሁሉም ሊበለጽጉ የሚችሉበትን አወንታዊ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ጤናማ፣ እና ህጋዊ የሥራ አውድ እና ባህል ለመመስረት፣ ለማክበር፣ እና ለመጠበቅ አስፈላጊው መረጃ እንዲኖራት/እንዲኖረው ለማድረግ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚሰጥ አስፈላጊ የሆነ ዓመታዊ ስልጠና ማለት ነው። ይህ በሜሪላንድ ህግ እና ደንብ JHC-RA መሰረት በህፃናት ላይ የሚፈፀም ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ለመለየትና ለመከላከል የሚያስፈልገውን ስልጠና ያካትታል።

E. *የአካባቢ የሕግ አስከባሪ መኮንኖች* ማለት በአሁኑ ጊዜ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የፖሊስ መምሪያ፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ሸሪፍ ጽ/ቤት፣ በሮክቪል ከተማ የፖሊስ መምሪያ፣ በታኮማ ፓርክ የፖሊስ መምሪያ፣ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ የስቴት አቃቤ ህግ ጽ/ቤት መካከል ተግባራዊ በተደረገ የመግባቢያ ሠነድ ላይ ከተሳተፉት የህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች መካከል ማንኛውም ኃላፊነት ያለው የህግ አስከባሪ ኦፊሰር ማለት ነው።

F. *የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) *ኮንትራክተር* ማለት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጋር በተደረገ ውል መሰረት ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አገልግሎት የሚሰጥ ግለሰብ ማለት ነው። እንደነዚህ ያሉ ግለሰቦች ለኮንትራክተሩ ተቀጥረው የሚሠሩ ሰራተኞች እና ኮንትራክተሩ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጋር ባለው ውል መሰረት የሚያስፈልገውን ስራ ለማከናወን የሚያሰማራቸውን ንዑስ የሥራ ተቋራጮች እና/ወይም ሌሎች የሥራ

ተቋራጮችን ሁሉ ያካትታል። በዚህ ደንብ ውስጥ የተገለጹት ከኮንትራክተር ጋር የተያያዙ የተወሰኑ ሂደቶች ኮንትራክተሮች ለሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

G. *የምንትጎምሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) *ሰራተኛ* ማለት በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተቀጠሩ ሠርተፊኬት ያላቸው ወይም የሌላቸው ሰራተኞች ማለት ሲሆን ይህም ተተኪ መምህራንን እና ጊዜያዊ ሰራተኞችን ያካትታል።

H. የMCPS *እጩ ተቀጣሪ* ማለት በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ስራ ለመቀጠር አመልካች ሲሆን የቃለ መጠይቅ ሂደቱን በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቀ(ች) እና ጊዜያዊ የቅጥር ማሳወቂያ የተቀበለ(ች) እና የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ለማጣራት በመጠባበቅ ላይ ያለ(ች) ማለት ነው። በሜሪላንድ ሕግ "ጊዜያዊ አዲስ ሠራተኛ" የሚለው ቃል የሥራ ታሪክ/ዳራ ማጣሪያው ሳይጠናቀቅ የተቀጠረ ሠራተኛ ማለት ነው።

I. የዩናይትድ ስቴትስ የፌዴራል ምርመራ ቢሮ (FBI) የእስር እና የክስ ሪከርድ ("Rap Back") ፕሮግራም ማለት የተፈቀደላቸው የመንግስት ኤጀንሲዎች የወንጀል ታሪክን ያለማቋረጥ እንዲከታተሉ የሚያስችል የፌዴራል የዳራ ፍተሻ ስርዓት/ሲስተም ማለት ነው። "Rap Back" ስለ አንድ ግለሰብ የወንጀል ድርጊት ታሪክ ላይ ስለሚከሰቱ ለውጦች ወዲያውኑ ለሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ያሳውቃል።

J. የሕፃናት ጥቃት እና ቸልተኝነትን ስለመገንዘብ (CAN *ስልጠና*) ማለት MCPS ደንብ JHC-RA ተግባራዊ ለማድረግ የተቋቋመ፣ *የሕፃናት ጥቃት እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ* ማለት ሲሆን ከሁሉም ሠራተኞች፣ ከሚመለከታቸው የሥራ ተቋራጮች/ኮንትራክተሮች እና ከሚመለከታቸው በጎ ፈቃደኞች የሚጠበቅ ግዴታ ነው።

K. (*ሪከርድ ያለባቸው*) የተመዘገቡ የወሲብ ጥቃት ወንጀለኞች *የተመዘገቡ የወሲብ ትቃት ወንጀለኞች* በተወሰኑ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሜሪላንድ ህግ እና MCPS ደንብ COA-RB፣መሰረት MCPS ንብረት ላይ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እንዲገኙ አይፈቀድላቸውም።

L. *ቁጥጥር በሌለ ሁኔታ ተማሪዎችን ማግኘት* ማለት በሜሪላንድ ህግ ላይ እንደተገለጸው፣ አንድ ግለሰብ በአካል ወይም ቨርቹዋል፣ በትምህርት ቀን ወይም MCPS በሚያከናውናቸው እንቅስቃሴዎች ወቅት በቀጥታ፣ያለ ቁጥጥር ከልጆች ጋር መገናኘት ይችላል/ትችላለች ማለት ነው።

M. በጎ ፈቃደኛ ማለት MCPS ደንብ IRB-RA፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ስለሚያገለግሉ በጎ ፈቃደኞች በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት MCPS ተማሪዎችን ለመደገፍ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን የሚለግሱ ግለሰቦች ማለት ነው።

II. የቀድሞ ታሪክ/ዳራ የማጣራት ሂደቶች

A. MCPS የሥራ ቅጥር እጩዎች እና ጊዜያዊ አዲስ ሰራተኞች

1. በሜሪላንድ ሕግ መሠረት፣ ሁሉም የሥራ ቅጥር እጩዎች የወንጀል ዳራ ማጣራት ሊደረግባቸው እና በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሥራ ከመጀመራቸው የመጀመሪያ የሥራ ቀን በፊት ውጤቱ MCPS መድረስ አለበት።

2. ሁሉም የሥራ ቅጥር እጩዎች በተጨማሪ ማድረግ ያለባቸው –

a) የወንጀል ጥፋቶችን፣ የፍርድ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት የክስ ሂደት መኖሩን የሚገልጽ የጽሑፍ መግለጫ ወይም ማረጋገጫ ማቅረብ፣ የወንጀል ተጠያቂነት የሌላቸው ውሳኔዎች ወይም የመጨረሻ ውሳኔ ሳይደረግባቸው በመጠባበቅ ላይ ያሉ የወንጀል ክሶች መኖራቸውን የሚያሳይ የጽሑፍ መግለጫ መስጠት፣ እና

b) በአመልካቹ የሥራ ታሪክ ላይ የተዘረዘሩትን አሠሪዎች በማነጋገር የሕፃናት ወሲባዊ ጥቃት እና/ወይም የጾታዊ ጥቃት ታሪክ/ዳራ ማጣራት።

c) በሜሪላንድ ሕግ መሠረት፣ MCPS ከላይ እንደተገለጸው መረጃ እና ሪከርዶች ማጣራት እስከሚጠናቀቅ ድረስ እና በሜሪላንድ ሕግ በተቀመጡት ተጨማሪ መስፈርቶች መሠረት፣ 60 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ የሥራ ቅጥር እጩን እንደ "አዲስ ጊዜያዊ ሠራተኛ" ሊቀጥር ይችላል። አንድ ግለሰብ እንደ ጊዜያዊ አዲስ ሠራተኛ ከተቀጠረ(ች) በኋላ 60 ቀናት ውስጥ፣ MCPS አስፈላጊውን የቅጥር ታሪክ/ዳራ ማጣራት መሰረት በማድረግ የጊዜያዊ ሠራተኛውን የቅጥር ሁኔታ ሊሰርዝ ይችላል።

3. ሁሉም የሥራ ቅጥር እጩዎች CPS ክሊራንስ ማጣራት በተሳካ ሁኔታ ማጠናቀቅ አለባቸው።

B. የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች

1. አንዴ ከተቀጠሩ በኋላ፣ MCPS ከላይ እንደተገለጸው ለሁሉም ሰራተኞች ቀጣይነት ያለው "Rap Back" ክትትል ያካሂዳል።

2. ሁሉም ሰራተኞች ዓመታዊውን ዲስትሪክት አቀፍ የህግ እና ሥነ ሥርዓት ማክበር ስልጠና ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል።

3. ሁሉም ሰራተኞች MCPS ደንብ GCC-RA መሠረት የእስራት፣ የወንጀል ክሶች፣ እና የተፈረደባቸውን ጥፋቶች ራሳቸው ሪፖርት ስለማድረጋቸተቀመጠውን ድንጋጌ ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

C. MCPS ኮንትራክተሮች/የሥራ ተቋራጮች

1. MCPS ኮንትራክተሮች የተመዘገቡ የወሲብ ወንጀለኞችን እና በጾታዊ ጥቃት፣ በልጆች ላይ በሚፈጸም የፆታ ጥቃት እና በሌሎች የዓመፅ/የረብሻ ወንጀሎች የተፈረደባቸውን ግለሰቦች ወደ MCPS ኮንትራት እንዳይገቡ የሚከለክለውን የሜሪላንድ ሕግ ያከብራሉ። በተጨማሪም፣ በሜሪላንድ የትምህርት አንቀጽ § 6-113፣ ድንጋጌ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተፈረደበ(ባ)ት ኮንትራክተር ወይም ጥፋተኛ መሆኑ(ኗ) ያመነ(ች) ወይም ጥፋተኛ አለመሆኑ(ኗ)ን በክርክር ላይ የሚገኝ ኮንትራክተር፣ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ያለ ቁጥጥር ተማሪዎችን እንዲያገኛቸው MCPS ኮንትራክተርን እንዳይመድብ ይከለክላል።

   a) እያንዳንዱ ኮንትራክተር ቀጥተኛ ሰራተኞቹን እና በኮንትራክተሩ ስር የሚሰሩ ሠራተኞችን በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ቤት ተቋም ውስጥ ሥራ እንዲሰሩ የተመደቡትን የማንኛውንም ንዑስ ኮንትራክተሮች እና/ወይም ሌሎች ኮንትራክተሮች ይህንን ግዴታ እንደሚያሟሉ የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ ይጠበቅበታል።

   b) በተጨማሪም የሥራ ተቋራጩ እና/ወይም ንኡስ ተቋራጮቹ ውሉ ላይ የተዘረዘሩትን ስራዎች ለማከናወን በሚጠቀሙበት የሠራተኛ ግብረሃይል ላይ ለውጦች ሲኖሩ ኮንትራክተሩ ይህንኑ ግዴታ በቀጣይነት መፈጸሙን ማረጋገጥ አለበት።

2. ያለ ቁጥጥር ተማሪዎችን የማግኘት እድል ያላቸው MCPS ተቋም ውስጥ የሚሰሩ ማንኛውም ኮንትራክተር ወይም የኮንትራክተሩ የሠራተኞች ግብረ ኃይል አባል

የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት፣CPS ክሊራንስ ማጣራት እና CAN ስልጠና ማጠናቀቅ አለባቸው።

3. MCPS ውስት የሚሠሩ ኮንትራክተሮች MCPS ጋር ላደረጉት ስምምነት እና/ወይም የመግባቢያ ስምምነት፣ (MOU) ውሎች እና ሁኔታዎች ተገዢ ናቸው።

4. DJA-RA ደንብ መሠረት የመስሪያ መሳሪያዎች ግዥ፣ አቅርቦቶች እና አገልግሎቶች ፣ የፋይናንስ አስተዳደር ክፍል (DFM) ውሎችን እና ሁኔታዎችን የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት፣ ይህም MOU ወይም ስምምነት ውስጥ የተቀመጡትን የቀድሞ ታሪክ/ዳራ እና የሥልጠና መስፈርቶችን ማስፈጸምን ጭምር ያካትታል።

   a) በዚህ ደንብ መሠረት የኮንትራክተሩን ብቁነት ለማረጋገጥ DFM የሠራተኞች ግብረ ኃይል እና የችሎታ ማበልፀግ ክፍል (DHRTM) ጋር ምክክር ያደርጋል።

   b) —እስከሚፈፀም ድረስ በኮንትራክተሩ የሠራተኞች ግብረ ኃይል ውስጥ ያለ(ች) አንድ ግለሰብ MCPS ንብረት ላይ ተመድቦ(ባ) ሥራ መጀመር አይችልም/አትችልም።

      1) የዚያ ግለሰብ የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት እና CPS ክሊራንስ ውጤቶች MCPS ከደረሰው በኋላ በዚህ ደንብ መሠረት ኮንትራክተሩ ብቁ እንደሆነ ይቆጠራል፤እና

      2) ግለሰቡ CAN ስልጠና ማጠናቀቁ(ቋ)ን ኮንትራክተሩ ለሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማረጋገጥ ይጠበቅበታል።

   c) ከላይ በአንቀጽ 4(b) የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟላ እና ያለ ቁጥጥር ከተማሪዎች ጋር የመገናኘት እድል ያለው/ያላት ግለሰብ MCPS የመለያ ባጅ ይሰጠዋል/ይሰጣታል።

   d) ለኮንትራክተሩ ባጅ ከተሰጠ በኋላ፣ አገልግሎቶቹ በሚከናወኑበት ሕንፃ ወይም ቦታ ኃላፊነት የሚመለከተው የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ የእያንዳንዱን ኮንትራክተር ባጅ የመፈተሽ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

e) ኮንትራክተር ባጅ ካልተሰጠው፣ አገልግሎቶቹ የሚከናወኑበት ሕንፃ ወይም ቦታ ኃላፊነት ያለው የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ በዚህ ደንብ እና MOU ወይም በስምምነቱ ላይ እንደተገለጸው፣ ግለሰቡ(ቧ) ሥራ ከመጀመሩ(ሯ) በፊት የማጣሪያ እና የሥልጠና መስፈርቶች መሟላታቸውን DFM ወይም ከፕሮጀክት አስተዳዳሪ ማረጋገጫ ማግኘት አለበት።

D. የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በጎ ፈቃደኞች

1. IRB-RA በትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙ በጎ ፈቃደኞች ደንብ ላይ እንደተገለጸው፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የበጎ ፈቃደኞችን ምርጫ፣ ምደባ፣ እና መተካትን በተመለከተ ውሳኔዎች የሚሰጡት በርእሰ መምህሩ ነው።

2. በጎ ፈቃደኞች ተማሪዎችን ያለ ቁጥጥር የማግኘት ሁኔታን መሰረት በማድረግ MCPS ስለ ቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት፣CPS ክሊራንስ ማጣራት እና CAN የስልጠና መስፈርቶችን ያዘጋጃል።

3. ርእሰ መምህራን/ተወካዮች/ወይም ሌሎች የበጎ ፈቃደኞች አስተባባሪዎች እንደሚከተለው፡ለበጎ ፈቃደኞች ሥልጠና የመስጠት ወይም የቀድሞ ታሪክ/ዳራ የማጣራት መስፈርቶችን ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው:-

   a) በዚህ ደንብ መሠረት አንድ በጎ ፈቃደኛ CAN ስልጠና እና/ወይም የቀድሞ ታሪክ/ዳራ የማጣራት ሂደት ማጠናቀቅ ይጠበቅበ(ባ)ት እንደሆነ መወሰን። በጎ ፈቃደኞች ተግባራቸውን ከመጀመራቸው በፊት መስፈርቶቹ ለበጎ ፈቃደኞች በተመጣጣኝ ጊዜ ውስጥ መገለጽ አለባቸው።

   b) በዚህ ደንብ መሠረት አስፈላጊ ከሆነ፣ የበጎ ፈቃደኛ ሠራተኛ CAN ስልጠና ጋር ያለውን ተገዢነት በቀጣይነት መከታተል።

   c) አስፈላጊ ከሆነ የጣት አሻራ ክፍያን መርዳት ጨምሮ የቀድሞ ታሪክ/ዳራ የማጣሪቱን ሒደት ለማጠናቀቅ አስፈላጊውን መረጃ ለበጎ ፈቃደኞች መስጠት።

4. በዚህ ደንብ መሠረት አስፈላጊ ከሆነ፣ አንድ በጎ ፈቃደኛ የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት ሒደት ካጠናቀቀ(ች) በኋላ፣"Rap Back" በቀጣይነት ክትትል ስለ

ማድረጉ DHRTM ኃላፊነት አለበት። DHRTM በዚህ ደንብ መሠረት ስለ ብቁነትን ከወሰነ በኋላ አንድ ግለሰብ በበጎ ፈቃደኝነት ለመሥራት ብቁ መሆን ወይም አለመሆን ለርእሰመምህር/ተወካይ/ወይም ለሌላ የበጎ ፈቃድ አስተባባሪ ያሳውቃል።

5. በሚጠበቀው የበጎ ፈቃደኝነት ተግባራት እና ያለ ቁጥጥር ተማሪዎችን የማግኘት ሁኔታ ላይ በመመስረት፣ ለበጎ ፈቃደኞች የሥልጠና እና የማጣራት መስፈርቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

a) ምንም አይነት ማጣራት ወይም ስልጠና ሳያስፈልግ – በጎ ፈቃደኞችን የመቆጣጠር ኃላፊነት ባላቸው የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ውሳኔ ያለ ቁጥጥር ተማሪዎችን የማግኘት እድሉ አነስተኛ የሆኑ ግለሰቦች CAN ስልጠናውን ማጠናቀቅ ወይም የዳራ ማጣራት እና CPS ክሊራንስ ማጣራት አይጠበቅባቸውም። እንደዚህ አይነት የበጎ ፈቃደኞች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ—

1) በትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ቀጥተኛ ቁጥጥር የሚከናወኑ የአንድ ጊዜ ዝግጅት በጎ ፈቃደኞች (ለምሳሌ፡- MCPS ትርኢት፣ የትምህርት ቤት ስብሰባ፣ ወይም በትምህርት ክፍል የሚደረግ ፓርቲ፤ በክፍል ንግግር ለማድረግ የተጋበዙ እንግዶች ወይም አንባቢ እንግዶች፤ የውድድር ዳኞች) የመሳሰሉትን ይመለከታል።

2) ከራሳቸው ልጆች ጋር በካፍቴሪያ ውስጥ ምሳ ለመብላት ወደ ትምህርት ቤቱ የሚመጡ ወላጆች/አሳዳጊዎች እንደ በጎ ፈቃደኞች አይቆጠሩም።

b) CAN ስልጠና ያስፈልጋል – ያለ ቁጥጥር ከተማሪዎች ጋር መገናኘት የማይችሉ ቢሆኑም ነገር ግን ከአንድ ጊዜ በላይ ወይም ለተወሰኑ ተግባራት በፈቃደኝነት የሚሰሩ በጎ ፈቃደኞች CAN ስልጠናውን ያለ ተጨማሪ የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራትን ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። የእነዚህ አይነት በጎ ፈቃደኞች ምሳሌ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

1) በትምህርት ዓመቱ ከአንድ ጊዜ በላይ በእረፍት ጊዜ፣ በካፍቴሪያ፣ እና ተማሪዎች በሚለቀቁበት ሠዓት ለመርዳት በክፍል ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ በፈቃደኝነት የሚሰሩ ግለሰቦች፣

2) ከቀኑ 7፡00 p.m. በፊት በመስክ ጉዞዎች ወይም በአትሌቲክስ ዝግጅቶች ላይ መገኘት ያለባቸው በጎ ፈቃደኞች፣

3) የክፍል ተማሪዎች ያሏቸው ወላጆች

4) መደበኛ ሠራተኞች ያልሆኑ ወይም ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ሠራተኞች (ለምሳሌ:- ማርቺንግ ባንድ)

c) CAN ስልጠና እና የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት ያስፈልጋል – በዘላቂነት እና/ወይም ያለ ቁጥጥር ተማሪዎችን የማግኘት እድል የመስጠት ኃላፊነት ያላቸው ግለሰቦች CAN ስልጠና፣ የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት እና CPS ክሊራንስ ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። የእነዚህ በጎ ፈቃደኞች ምሳሌ የሚከተሉትን ያካትታል:-

1) የሌሊት የመስክ ጉዞ አጃቢ በጎ ፈቃደኞች፣ በስሚዝ ሴንተር የሚከናወኑ የውጪ ፕሮግራሞችን የሚረድቱን ጨምሮ፤

2) ከቀኑ 7፡00 p.m., በኋላ ወይም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ውጭ በሚደረጉ ጉዞዎች ላይ የሚረዱ በጎ ፈቃደኞች፤

3) በጎ ፈቃደኞች በቨርቹዋል ትምህርት ላይ የሚሰማሩ ከሆነ አንድ በጎ ፈቃደኛ በክፍል ውስጥ በትናንሽ ቡድን ለሚሠሩት እንቅስቃሴ ኃላፊነት ሊኖረው/ሊኖራት ይችላል።

4) በአበል የሚሠራ አሰልጣኝ ቁጥጥር የሚሠሩ እና MCPS የበጎ ፈቃድ አሰልጣኝ የአትሌቲክስ ማመልከቻ እና ውል ያጠናቀቁ በጎ ፈቃደኛ አሰልጣኞች።

3. በዚህ ደንብ መሠረት በጎ ፈቃደኛ ሰው CAN ስልጠና መውሰድ የሚጠበቅበ(ባ)ት ከሆነ፣ በጎ ፈቃደኛው(ዋ) በየዓመቱ CAN ስልጠና ማጠናቀቅ ይጠበቅበ(ባ)ታል።

4. ከላይ እንደተገለጸው የበጎ ፈቃደኞች CAN ስልጠና፣ የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት እና CPS ክሊራንስ በማንኛውም የበጎ ፈቃደኝነት ተግባራት ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከመሳተፋቸው በፊት በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በኩል መጠናቀቅ አለባቸው። የምሽት ወይም የማታ አዳር የመስክ ጉዞዎች ላይ የሚረዱ እና የሚከታተሉ በጎ ፈቃደኞች ከጉዞው አስቀድሞ ቢያንስ ከሰባት (7) የስራ ቀናት በፊት ሁሉንም መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።

5. ሁሉም በጎ ፈቃደኞች የትምህርት ቤት ንብረት ሲገበኙ ደንብ ABA-RB፣ የትምህርት ቤት ጎብኚዎች ድንጋጌ መሠረት በአሜሪካን ስቴት ወይም በዲስትሪክት ኦቭ ኮሎምቢያ የተሰጠ የፎቶ መታወቂያ ካርድ (ለምሳሌ፡- የመንጃ ፈቃድ) ቅጂ/ፎቶ ኮፒ ማቅረብ አለባቸው። አንድ በጎ ፈቃደኛ በአሜሪካን ስቴት ወይም በዋሽንግተን ዲሲ የተሰጠ የፎቶ መታወቂያ ካርድ ማቅረብ ካልቻለ(ች)፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኛ የግለሰቡ(ቧ)ን ስም VMS ኪዮስክ ላይ በእጅ ይጽፋል፣ ከዚያም ዩ.ኤስ የፍትህ ዲፓርትመንት ብሔራዊ የወሲብ ጥቃት ወንጀለኞች የተመዘገቡበት የመረጃ ቋት ድረ ገጽ ላይ ይፈልጋል።

6. እዚህ ላይ እንደተገለጸው አሁን ያሉት የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት ሂደቱን የጨረሱ ሰራተኞች እንደ በጎ ፈቃደኛ ሆነው ለማገልገል እንደ አዲስ የጣት አሻራ ዳራ ማጣሪያ ማጠናቀቅ አይጠበቅባቸውም። እነዚህን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ርእሰ መምህሩ(ሯ) DHRTM ጋር ማረጋገጥ አለበ(ባ)ት።

7. ስለ አንድ የበጎ ፈቃደኛ ሰው የበፊት ታሪክ/ዳራ ማጣራት መረጃ ለመቀበል የተፈቀደለት የተመደበ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ብቸኛው የትምህርት ቤት ሰራተኛ ባልደረባ ሲሆን ይህም ለሌሎች ያልተፈቀደላቸው ሰራተኞች ወይም ለሌሎች በጎ ፈቃደኞች መረጃውን ማጋራት የለበትም።

8. ጥቃት በመፈፀም የተመዘገቡ ሰዎች በማንኛውም ሁኔታ በበጎ ፈቃደኝነት MCPS ጋር መሥራት አይፈቀድላቸውም።

E. ከጡረታ በኋላ/የተቀጠረ(ች)። ቀደም ሲል MCPS ውስጥ ተቀጥረው የነበሩ እና ጡረታ የወጡ ወይም በአገልግሎት እረፍት ምክንያት አቋርጠው የነበሩ እና እንደገና ወደ ሥራ ተመልሰው የሚቀጠሩ ከሆነ እንደማንኛውም ሠራተኛ በዚህ ደንብ መሠረት አዲስ የበፊት ታሪክ/ዳራ ማጣራት እና CPS ክሊራንስ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ይህ መደረግ ያለበት ካቋረጡበት ጊዜ አንስቶ ዳግም የሚቀጠሩበት ወቅት የሚወስደው ጊዜ አንድ (1) ቀን ብቻ ቢሆንም እንኳ መደረግ አለበት።

F. ተተኪ/ጊዜያዊ ሠራተኛ። ተተኪ ሠራተኞችና ጊዜያዊ ሠራተኞች ልክ እንደ ሥራ ተቀጣሪ እጩዎችና ሠራተኞች ተመሳሳይ የማጣራት ሂደት ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል።

G. አጫዋች ዳኞች/የአትሌቲክስ ኃላፊዎች። ሁሉም የአትሌቲክስ ባለስልጣናት እና ዳኞች ኮንትራክተሮች ሲሆኑ በየራሳቸው የመግባቢያ ስምምነት ላይ ወይም በተፈራረሙት ስምምነት ውስጥ ለተቀመጡት የበፊት ታሪክ/ዳታ የማጣራት መስፈርቶች ተገዢ ናቸው።

H. ተማሪ መምህራን። ተማሪ መምህራን ያለ ምንም ቁጥጥር ከልጆች ጋር የመገናኘት ወይም የተማሪዎችን መረጃ የማግኘት እድል ከማግኘታቸው በፊት የበፊት ታሪክ/ዳራ ማጣራት ክንውን፣ CPS ክሊራንስ ማግኘት እና የዲስትሪክት አቀፍ ሥነ ስርዓት እና ደንብ፣ መመሪያ የማክበር ስልጠና ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪ አስተማሪን የሚያስተናግደው ትምህርት ቤት ወይም ቢሮ ይህ ደንብ መከበሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

I. የሥራ ተለማማጅ ተማሪዎች/Interns MCPS ውስጥ በሥራ ተለማማጅነት ለተወሰነ ጊዜ ጊዜያዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተማሪዎች (ይህ ለሶስተኛ ወገን የሥራ ተለማማጅ የሆኑ MCPS ተማሪዎችን አያካትትም) ምንም አይነት ቁጥጥር የማይደረግበት ከልጆች ጋር መገናኘት ወይም የተማሪ መረጃ ከማግኘታቸው አስቀድሞ የበፊት ታሪካቸውን/ዳራ ማጣራት፣ CPS ክሊራንስ፣ እና ዲስትሪክት አቀፍ ደንብ የማክበር ስልጠና ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል። የሥራ ተለማማጅ ተማሪን የሚያስተናግደው ትምህርት ቤት ወይም ቢሮ ይህ ደንብ መከበሩን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

J. ከላይ እንደተገለጸው፣ የትምህርት ቤትን ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ ያለባቸው የፖሊስ ዩኒፎርም ለብሰው የሚሰሩ የአካባቢ ህግ አስከባሪ መኮንኖች እንደ ሁለተኛ ደረጃ ተቀጣሪ ይቆጠራሉ።

1. በሞንትጎመሪ ካውንቲ የፖሊስ መምሪያ፣ በሸሪፍ ዲፓርትመንት ወይም በሌላ የከተማ አስተዳደር/ማዘጋጃ ቤት የሚከፈላቸው MCPS ውስጥ እንደ ማህበረሰብ ተሳትፎ ኦፊሰሮች (CEOs) ህግ የማስከበር ተግባራትን እንዲያከናውኑ የተመደቡ ሰራተኞች እንደ CEO ተግባራትን ለማከናወን MCPS ተጨማሪ የጣት አሻራ ወይም CPS ክሊራንስ ማጣራት እንዲያደርጉ አይጠበቅባቸውም። CEOs እንደሌሎቹ CAN ስልጠና እንዲወስዱ አይጠበቅባቸውም።

2. ከላይ እንደተገለጸው፣ በትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ፣ በዝግጅት ደህንነት ጥበቃ፣ ወይም ተዛማጅ የደህንነት ጥበቃ ተግባራትን የሚያከናውኑ የፖሊስ ዩኒፎርም ለብሰው MCPS ውስጥ የሚሠሩ እና MCPS የሚከፈላቸው የአካባቢ የህግ አስከባሪ መኮንኖች፣ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የፖሊስ ዲፓርትመንት፣ የሸሪፍ ዲፓርትመንት፣ እና በሌሎች የከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤቶች አስቀድመው

ከተቀመጡት መስፈርቶች ውጭ ተጨማሪ የበፊት ታሪካቸው/ዳታ እና የጣት አሻራ ማጣራት ሂደቶችን እንዲያካሂዱ አይጠበቅባቸውም። አንድ ኦፊሰር ጡረታ ሲወጣ፣ ከስራ ሲለቅ፣ ወይም በመምሪያው የተሰጡትን ተግባራት ለማከናወን ብቁ ካልሆነ ከዲፓርትመንቱ ኃላፊነት የሚመለከተው ሰው ለሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማሳወቅ ይጠበቅበታል።

3. ከላይ እንደተገለጸው፣ MCPS ውስጥ ከትምህርት ቤት ደህንነት ጋር ያልተያያዙ ሌሎች የሚከፈልባቸውን ተግባራት (ለምሳሌ፡- የሚከፈልበት ስልጠና መስጠት ወይም ምትክ ማስተማር) ማከናወን የሚፈልጉ የአካባቢ ህግ አስከባሪ መኮንኖች MCPS የበፊት ታሪካቸውን/ዳራ የማጣራት ሒደት፣ CPS ክሊራንስ ማጣራት እና ለተፈለገው ቦታ የሥልጠና መስፈርቶችን ማጠናቀቅ አለባቸው።

K. ከመደበኛ የተመደቡበት ቦታ ውጭ በሚደረጉ ዝግጅቶች ከተማሪዎች ጋር የሚገናኙ ጎልማሳ ሰዎች።

1. ተማሪዎች በጣምራ ምዝገባ ፕሮግራሞች በኮሌጅ ግቢዎች ውስጥ ትምህርት መከታተል ወይም MCPS ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት ከትምህርት ቤት ግቢ ውጭ ከውጭ አካል ወይም ተቋም ጋር ተግባራዊ ልምምድ ላይ መሳተፍ ይችላሉ። ድርጅቱ ከህግ እና MCPS የወንጀል ዳራ ፍተሻ መስፈርቶች ጋር የሚጣጣም የበፊት ታሪክ/ዳራ ማጣራት እና የጣት አሻራ የማጣራት ሂደት ሊከናወን ይገባል፣ ወይም ተማሪዎችን ለመቆጣጠር የሚመለከታቸው ሰራተኞች MCPS የጣት አሻራ ዳራ ፍተሻ እና CPS ክሊራንስ ማጠናቀቅ አለባቸው።

2. በተጨማሪም፣ በፕሮግራም ወይም በኢንተርንሺፕ ምክንያት የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎችን የሚያስተምሩ ወይም የሚቆጣጠሩ ተሳታፊ ከሆኑ የውጭ ኤጀንሲዎች ወይም ተቋም የሚመጡ ሰራተኞች CAN ስልጠና ማጠናቀቅ ይጠበቅባቸዋል።

L. "Rap Back" አማካኝነት የሚደረግ ቀጣይነት ያለው ክትትል

1. በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአንድን ግለሰብ የበፊት ታሪክ/ዳራ ማጣራት ሲጠናቀቅ፣"Rap Back" ቋት ውስጥ ይመዘገባል። በዚህ ደንብ ውስጥ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት፣ "Rap Back" ቋት ላይ ከተመዘገበ በኋላ እና ግለሰቡ(ቧ) በተቀጠረ(ች)በት ሥራ፣ በበጎ ፈቃደኝነት

አገልግሎት፣ ወይም MCPS ጋር በኮንትራት እስከቆየ(ች) ድረስ፣ የግለሰቡ(ቧ) የወንጀል ታሪክ "Rap Back" በኩል ክትትል ይደረጋል።

2. ግለሰቡ(ቧ) አገልግሎት መስጠት ካቆመ(ች) ወይም MCPS የወንጀል ታሪካቸውን መከታተል አስፈላጊ ካልሆነ፣ DHRTM ድንጋጌ መሠረት በተመጣጣኝ ጊዜ ውስጥ MCPS የግለሰብን ስም "Rap Back" ከመረጃ ቋት ውስጥ ያስወግዳል።

3. አንድ ግለሰብ አገልግሎት ሲያቋርጥ/ስታቋርጥ "Rap Back" አማካኝነት የሚደረገውን ክትትል MCPS እንዲያቆም ወደ DHRTM በጽሑፍ መጠየቅ ይችላል/ትችላለች።

## III. ብቁ አለመሆን

A. MCPS አንድ ሠራተኛ፣ እጩ ተቀጣሪ፣ ኮንትራክተር፣ በጎ ፈቃደኛ፣ ወይም ሌላ ግለሰብ "ብቁ መሆን" ወይም "ብቁ አለመሆንን" ለመወሰን የበፊት ታሪክ/ዳራ ማጣራት የተደረገበትን፣ CPS ክሊራንስ የተጣራበትን፣ እና "Rap Back" ክትትል የተደረገበትን ውጤት ይጠቀማል። DHRTM እንደዚህ አይነት የብቁነት ውሳኔዎችን የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

B. የብቁነት ውሳኔዎች የሚወሰኑት የግለሰቡ(ቧ) የቀድሞ ታሪክ/ዳራ ማጣራት የተደረገበት ውጤት እና "Rap Back" ክትትል ውጤት እና/ወይም ሌላ ተዛማጅ ሰነዶችን ወይም መረጃዎችን በተናጠል ግምገማ ተደርጎ ነው። MCPS ለህዝብ ይፋ የተደረጉ መረጃዎችን እና MCPS የሰራተኛ ማህደር/ፋይሎች ውስጥ የሚገኙ መረጃዎችን ጭምር መገምገም ይችላል።

C. በሜሪላንድ ሕግ መሠረት፣ በወንጀል ድርጊት በጥፋተኝነት የተፈረደበ(ባ)ት ግለሰብ MCPS ውስጥ ሥራ ለመቀጠር ብቁ አይደለ(ች)ም።

D. ዳራ ምርመራ ማድረግ ያለበት ማንኛውም በጎ ፈቃደኛ የወንጀል ክስ ካለበት ለበጎ ፈቃደኝነት ሥራ ብቁ እንዳልሆነ(ች) ይቆጠራል። እንደ አጠቃላይ መመሪያ:- ክስ ያለባቸው፣ የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጣቸው፣ ወይም ሌላ ስጋት የሚያስከትሉ ግለሰቦች፣ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጋር በጎ ፈቃደኛ ወይም ኮንትራክተር ሆነው ለማገልገል ብቁ አይደሉም።

E. የቀድሞ ታሪካቸው/ዳራ ማጣራት እና/ወይም CPS ክሊራንስ ማጣራት 1) አደንዛዥ ዕፅ ወይም ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮችን ስርጭትን የሚመለከቱ ማናቸውም

ጥፋቶችን የሚያመለክት መረጃ፣ 2) በደል በማድረግ ወይም በቸልተኛነት ወይም "ጥቆማ የተደረገበ(ባ)ት" የልጅ ጥቃት ወይም ቸልተኝነት መረጃ ከተገኘ እና CPS ክሊራንስ ከተጠናቀቀ በኋላ፤ ወይም 3) በሜሪላንድ የተብራራ ሕግ (የሜሪላንድ ሕግ)፣ የትምህርት አንቀጽ፣ § 6-113 ውስጥ ከተቀመጡት ወንጀሎች ጋር በተያያዘ በቀጠሮ ላይ ያሉ ክሶች ወይም የእስር ትዕዛዝ ከተገኘ፣ MCPS ውስጥ የማገልገል ብቁነትን ለመወሰን እያንዳንዱን ሁኔታ በተናጠል ይፈትሻል።

F. ከላይ (C) እና (E) ላይ ከተዘረዘሩት የወንጀል ጥፋቶች እና CPS ግኝቶች በተጨማሪ፣ የአንድ ግለሰብ ጉዳይ በዝርዝር ከተገመገመ በኋላ፣ እንደ ጥፋቱ ሁኔታ እና ድግግሞሽ፣ እንደ ወንጀሉ ሁኔታ ወይም ክሱ ከተከፈተበት ጊዜ ጀምሮ ባለው ጊዜ ውስጥ፤ እና ግለሰቡ(ቧ) MCPS ውስጥ በፈቃደኝነት ለመቀጠር ወይም ለመመደብ የማያስችሉ ሌሎች ምክንያቶች፣ በተለይም MCPS ተማሪዎችን ደህንነት የሚመለከቱ ወንጀሎች ከሆኑ ለመቀጠር ብቁ አይሆኑም።

G. ከላይ ያልተዘረዘሩ ሌሎች ጥፋቶችም MCPS ጋር ከመቀጠር የሚታገድበት ሁኔታን ሊያስከትሉ ይችላሉ።

H. DHRTM አንድ በጎ ፈቃደኛ MCPS ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከማገልገል የሚያግድ አዲስ ክስ ወይም ጥፋተኛ መሆኑን የሚገልጽ የወንጀል ሪከርድ ከደረሰው/ካገኘ፣ DHRTM ግለሰቡ በፈቃደኝነት ለመሥራት ብቁ እንዳልሆነ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ማሳወቅ አለበት፣ እና የሚመለከተው ኃላፊም በጎፈቃደኛ ሠራተኛው ሁሉንም የበጎ ፈቃድ እንቅስቃሴዎች ወዲያውኑ እንዲያቆም የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

IV. የሥራ እጩዎችን እና ሠራተኞችን የሚመለከት ሂደቶች

A. ሥራ የሚቀጠሩ እጩዎች እና ሠራተኞች እዚህ ላይ የተዘረዘሩት ሁሉም አስፈላጊ እርምጃዎች እስኪጠናቀቁ ድረስ እና አንድ ግለሰብ በዚህ ደንብ መሠረት እንዲሠራ DHRTM ፈቃድ እስኪገኝ ድረስ ሥራ መጀመር አይችሉም።

B. በዚህ ደንብ መሠረት እጩ ተቀጣሪ ወይም ሠራተኛ ብቁ እንዳልሆነ(ች) ሲወስን፣ DHRTM ለግለሰቡ በማሳወቅ ምላሽ የመስጠት እድል ይሰጠዋ(ታ)ል።

C. MCPS አንድ ሠራተኛ ወይም እጩ ተቀጣሪ ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ/እንድታቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፣ ይህም የክስ ሰነዶችን ቅጂ እና ከዚያ በኋላ የሆነውን ማንኛውንም የወንጀል ክስ ውሳኔን ያካትታል።

D. MCPS ውስጥ ሥራ ለመቀጠል ወይም የቅጥር ሂደቱ የመቀጠል ሁኔታ የሚወሰነው በፍርድ ቤት እና በፖሊስ መዝገቦች ላይ በተንጸባረቀው የወንጀል ባህሪ ሁኔታ እና በግለሰቡ ምላሽ ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ ነው።

E. በቅጥር ማመልከቻ ላይ ሆን ብለው የወንጀል ባህሪን በተሳሳተ መንገድ የገለጹ እጩ ተቀጣሪዎች ወዲያውኑ ከታሰቡበት የመቀጠር ሂደት ይሠረዛሉ።

F. ሆን ብለው የወንጀል ድርጊትን ባህሪ በተሳሳተ መንገድ የገለጹ ወይም GCC-RA ደንብ መሰረት የተወሰኑ የወንጀል ባህሪያትን ሪፖርት ያላደረጉ ሰራተኞች፣ ሰራተኞች ስለ እስራት፣ የወንጀል ክሶች፣ እና ጥፋቶች እራሳቸው ሪፖርት ስለማድረግ፡ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል።

G. የጣት አሻራ የበፊት ታሪካቸው/ዳራ ማጣራት እና CPS ክሊራንስ ውጤቶች ቅጂ በሠራተኛው(ዋ) ማህደር ውስጥ ተመዝግቦ ይቀመጣል።

V. ክፍያዎች

A. የሥራ እጩዎች እና ኮንትራክተሮች – የሥራ እጩዎች እና ኮንትራክተሮች የቀድሞ ታሪካቸውን/ዳራ ማጣራት የሚያስፈልገውን ወጪ በሙሉ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው። ለሥራ እጩዎች እና ለኮንትራክተሮች የበፊት ታሪክ/ዳራ ማጣራት የሚያስፈልጉ ክፍያዎችን የሚወሰነው DHRTM ነው።

B. በጎ ፈቃደኞች – በቦርድ ፖሊሲ ABC፣ *የቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ትብብር* ላይ እንደተገለጸው፣ ቦርዱ ሁሉም ወላጆች/አሳዳጊዎች በልጆቻቸው ትምህርት ላይ እንዲሳተፉ ያበረታታል እንዲሁም ንቁ ተሳትፎአቸውን የሚያደናቅፉ እንቅፋቶችን ለማስወገድ በትጋት ይሰራል።

1. የጣት አሻራ መረጃ የማግኘት ወጪ የወላጅ/የአሳዳጊ የበጎ ፈቃደኝነት እድልን አያደናቅፍም።

2. የጣት አሻራ መረጃ የማግኘት ወጪዎችን በተመለከተ የገንዘብ ድጋፍ መረጃ ማግኘት እና ከሚመለከተው የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሱፐርቫይዘር የሥራ ባልደረባ ጋር መነጋገር ይቻላል።

VI. የጣት አሻራ የሚሰጥበት ቦታ እና ተዛማጅ መረጃዎች

A. እዚህ ላይ በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፣ የዳራ ፍተሻዎች MCPS ድረ ገጽ ላይ በተገለጹት ቦታዎች መጠናቀቅ አለባቸው።

B. የበፊት ታሪክ/ዳራ የማጣራት ሒደት ላይ የግል መረጃዎችን (የማህበራዊ ዋስትና ቁጥርን/ሶሻል ሰኩሪቲ ነምበር ጨምሮ)፣ የጣት አሻራ እና ፎቶግራፍ ይፋ መደረግ ይኖርበታል። አንድ በጎ ፈቃደኛ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር/ሶሻል ሰኩሪቲ ነምበር ከሌለው፣ ትምህርት ቤቶች DHRTM ሌላ አማራጭ ሂደት መጠየቅ ይችላሉ።

C. MCPS የጣት አሻራ የሰጡ ሁሉም ግለሰቦች ስለ ወንጀል ዳራ ሪፖርት ቅጽ ማግኘት እንዲቻል መፈረም እና የጽሑፍ ፈቃድ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** 34 U.S. Code §20962 - Schools Safety Acquiring Faculty Excellence Act of 2006 ("Schools SAFE Act"); Annotated Code of Maryland (MD Code), Education Article, §6-113, §6-113.1, and §6-113.2; MD Code, Family Law Article §5-551-§5-553; MD Code, Criminal Procedure Article, §11-722; MD Code, Criminal Law Article, §3-307, §3-308, §3-602, and §14-101; Code of Maryland Regulations 13A.15.02.07B(1)-(11)

**ስለ ደንቡ ታሪክ፡-** አዲስ ደንብ ኖቬምበር 13, 2025 ፀድቋል፣ ከጃንዋሪ 1, 2026 ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፡-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜኘት መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኸውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተሟለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይሟለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ኦክቶበር 2025